# የተቃዋሚዎች እንቆቅልሽ

*ተሻለ ለማ ቱሬ*

*ከሻሸመኔ*

አሁንስ ሁለቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግራ ገብቷቸው ግራ አጋቡን ::ቅንጅትም ሆነ ህብረቱ ጭራቸው አልያዝ ብሎናል:: ዛሬ ያሉትን ነገ አይደግሙም:: ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያሉትን አቶ ልደቱ ያፈርሱታል:: ዶ/ር መረራ ያነሱትን ዶ/ር በየነ ያጣጥሉታል:: የኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ነገርማ አይነሳ! ሰው ያለውን አይደለም ራሳቸው የተናገሩትን እንኳ አይደግሙትም::

አንድ ወዳጄ የተቃዋሚዎች የቅርብ ሰው እንደሆነ ይታወቅልኝ ይህ ሁኔታ የቅንጅት አመራሮችን ሳይቀር አንገት አስደፍቷል ብሎኛል:: ምን ያደርጋል ወትሮም ውሳጣቸው በእውነተኛ መነቃቀፍ ላይ ያልተመሰረተ ስለሆነ እየተሞዳምዱ መሄድን መርጠዋል:: ይኸው ወዳጄ እንደነገረኝ ኢንጅንር ኃይሉ የመጣላቸውን የሚናገሩ አኩራፊ ሰው በመሆናቸው ነው የአመራር ቦታ እንኳ የተሰጣቸው:: ለነገሩ አቶ ልደቱን አይቤክስ ሆቴል በተካሄደ ስብሰባ ላይ "ያልተፃፈ አታንብ" ብለው በትህትና /እንደ እንጂነሩ ባህሪ/ ተናግረውት የለ::

የዛሬው ጽሁፌ አላማ የፖለቲከኞቻችን ስብዕና መመርመር አይደለም:: ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው ቅንጅትና ህብረት ፖስታና ቴምብር ነን እያሉ ቢናገሩም ልዩነታቸው የሰማይ እና የምድር ያህል ነው:: በኢህአዴግ ላይ ካላቸወ ጥላቻ በተጨማሪ እነዚህን ኃይሎች የሚያመሳስላቸው ባሉት የማይፀኑ መሆናቸው ነው:: ኢንጂነር ኃይሉ "ኢትዮጵያውያን ሁለት መልክ አላቸው " ሲሉ ለቢቢሲ የሰጡት መግለጫ ለእነሱ መስራቱን እርግጠኛ ነኝ::

አቶ ኃይሉ ከጋዜጠኛው ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ በሰኔ አንድ ሁከት ፓርቲያቸው እንደሌለበት ሲናገሩ አንድም ነገር አላቅማሙም:: ጉድና ጅራት ከሁዋለ ነው እንደሚባለው ኢንጀነሩ ለመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ማዕከላዊ ምክር ቤት ባደረጉት ንግግር ግን በመርካቶ አውቶብስ ተራ እና መሳለሚያ ወዘተ በተነሳው ሁከት የሞቱት የድርጅቱ ወረቀት በታኞች፤ በየቤቱ ቅንጅትን ምረጡ ሲሉ የነበሩ ሰዎች እንደሆኑ ገለጹ::

ኢንጅነር ኃይሉ ለኢትኦጵ ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ የምርጫ ቅሬታዎች ማጣራት እንዲካሄድ ሰኔ 1997 በቅንጅት ህብረትና እና ኢህአዴግ መሀከል ስምምነት ቢደረስም " ስምምነት ብሎ ነገር የለም " አሉ:: ቅንጅት ከምርጫ ውጤት መገለጽ በኋላ

ፍርድ ቤት በሄደበት ማግስት አቶ ኃይሉ ሻውል ፍርድ ቤት መሄድ የማይታሰብ እንደሆነ ተናግረዋል።

የአቶ ኃይሉን በዚህ ላበቃና አቶ ልደቱ አያሌውም ቢሆን ህብረቱ እና ቅንጅቱ እንጣመር ማለታቸውን የሰሙት ውለው አድረው ነው።

በነገራችን ላይ የቅንጅት እያንዳንዱ አመራር ያነሳውና የጣለውን ማንሳት ቢፈለግ ይህ ገጽ አይበቃውም ስለዚህ ወደ ህብረት እንሂድ።

ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ የምርጫውን ውጤት ተቀብሎ ወደ ፓርላማ ለመግባት የሰጡት ምሳሌ "ህፃን ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል" የሚል ነበር። እንደ እኔ ግን አንድ ለእናቱ በሚመስል መልኩ ፓርላማው ውስጥ በተለያዩ ውሳኔዎች ላይ በሚያንፀበርቁት ግልጽና ትህትና የተሞላበት አቋማቸው የማከብራቸው ዶ/ር በየነ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማግስት 52 የሳቸው ፓርቲ አባሎች ፓርላማ ተከትለው ይገባሉ እና ሊያለቅሱ ሳይሆን ሊደሰቱ ይገባል። ከሳቸው በተቃራኒ ደግሞ ዶ/ር መረራ ፓርላማ አንገባም ባይ ናቸው። ዶ/ር መረራ" የመሬት አንቀጥቀጥ ህዝባዊ ማዕበል" አቀንቃኝ በመሆናቸው ፓርላማ አንገባሞ ቢሉም በአንድ ፓርቲ ወስጥ የዚህን አይነት የአቋም መለየት ምን ይባል ይሆን?

እዚህ ላይ ቅንጅት የአዲስ አበባ አስተዳዳሪዎችን መርጦ ካበቃ በኋላ /እገረመንገዴን እንኳን ደስ ያላችሁ ብያለሁ/ ህብረቱም አሸናፊ የፓርላማ አባላቱን ውስጥ ውስጡን ወደ ም/ቤቱ ለመግባት ተዘጋጁ ባሉበት ሁኔታ የሚያቅማሙበት ምክንያት ምንድ ነው የሚለው ነው።

ታቃዋሚዎች በምረጡኝ እንቅስቃሴ ወቅት ገዢው ፓርቲ ለማጭበርበር መዘጋጀቱን ቢናገሩም ራሳቸውም አለም አቀፍ ማህበርሰብ ብሎም ኢህአዴግ ከጠበቁት ውጭ መቀመጫ ማግኘት ችለዋል። በሌላ በኩል ምርጫው ከተጭበረበረ "በመሬት አንቀጥቅጥ አመጽ ገዢውን ፓርቲ ለማባረር" የነበራቸው ህልም መና ቀርቷል።

እንደጆርጅያና ዩክሬንም በአበባ እና አትክልት የተሰየሙ አብዮቶችን በማድረግ በህዝቡ እና በምዕራቡ አለም ግፊት የስልጣን ዕረካብ ለመቆናጠጥ የነበራባቸው ዕቅድም ከውጥኑ መክኗል። የኢትዮጵያ ህዝቦችም ሆኑ አለም አቀፉ ማህበረሰብ ፓርላማ ግቡና ታገሉ የሚለው ለድርድር የማይቀርብ ምላሻቸው ሆኖ ተገኝቷል።

ሁለቱ ፓርቲዎች ጥቅምት የሚመሰረተው መንግስት ዕውን እስኪሆን ድረስ " ጭር ሲል አንወድም" ማለታቸው አይቀርም:: ከወዲሁ ውጤት ተቀብለው ፓርላማ እንሳተፋለን ቢሉ ለደጋፊዎቻቸው የገቡት የማይተገበር ቃልኪዳን ሀቅ ስለሚተናነቃቸው የምንችለውን ያህል አድርገናል ለማለት ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ ናቸው:: አይታለምም ባይባልም አይሳካም እንጂ በኢህአዴግ ላይ የተቻለውን ያህል ጫና በማብዛት ማስተዛዛኛ እንኳ ስልጣን ማግኘት የሚለው ሌላው የተቃዋሚዎች ታክቲክ ነው::

ሌላው ሰሞነኛ እንቆቅልሽ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት /ኢዲኃህ/ በሜሪላንዱ ሰብሰባ ያሳለፈወ ውሳኔ ነው::ለተቃዋሚ መሪዎቹ ቀረቤታ ያላቸው ወዳጆቹ እንዳሉኝ ህብረቱ ከቅንጅቱ ቀድሞ ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ የሚል አቋም ይዟል::

የህብረቱ የምርጫ ስትራቴጂስት አቶ ነገደ ጉበዜ የሚመሩት መኢሶን በሜሪላንዱ ስብስባ ህገ - መንግስቱን በኢ-ህጋዊ መንገድ እንቀይር የሚል አቋማቸውን ማፅናታቸው ነው የገለፁት::

መኢሶን በዚሁ ስብሰባ ላይ በአጀነዳነት እንዲያዝለት ሐምሌ 1997 ያዘጋጀውን ሠነድ አቅርቧል:: ሠነዱ የግንቦት 7 ምርጫን ገምግሞ ወደፊት ምን ይደረግ የሚል ነው:: የግንቦት ሰባት ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ ለተወካዮቹ ይሁንታውን መስጠቱን ወዳጅም ጠላትም የመሠከረበት ስለሆነ የመኢሶንን የግምገማ ትተን የቀጣይ እርምጃውን ትልም እንቃኝ::

መኢሶን በሰነዱ ገጽ 3 ላይ ባቀረበው ሃሳብ መሰረት ቀጣይ ዕቅዱ የብሄራዊ ዕርቅ ዕውን ለማድረግ የሚያስችል መንግስት መመስረት ነው:: ይህ መንግስት ታድያ የሽግግር ስርዓቱን መምራት አይፈቀድለትም:: በሠነዱ መሠረት የመኢስን ስጋት ይህን አቋም እንኳን ኢህአዴግ፣ ቅንጅት ላይቀበለው ይችላል የሚል ነው:: የሚለውን ቃል በቃል ላስቀምጥ :-

የሚያስፈልግን የሽግግር መንግስት በሽግግር ዘመን በፕሮግራማችን
የተዘረዘረሩትን የዲሞክራይዜሽንና የብሔራዊ እርቅ ተግባራት እውን ለማድረግ
የሚካሄደውን ጥረት የሚያግዝ መንግስት ነው::------- ይህ ኃላፊነት ለብሄራዊ ዕርቅ
ኮሚሽን መተው አለበት:: በዚህ ሂደት ኢህአዴግና ቅንጅት ላይስማሙ ይችላሉ::

ኢህአዴግ እንኳን አሸንፎ ተሸንፎ ከናንተ ጋር መንግስት አልመሰርትም ብሏል፤ መኢሶኖች ከቅንጅት ጋር ምን ይሆን ድብብቆሹ? ለነገሩ በሜሪላንዱ ሰብሰባ ከቅንጅት ጋር በቀጣይ በሚኖረው ትብብር /ቢያንስ ፀረ- ኢህአዴግነት/ላይ ያው ልዮነት የተነሳው የአደባባይ ሚስጥር ይህ ነበር።

ዶ/ር ነገደ በዚህ ሰነዳቸው ተቃዋሚዎች የአብላጫ ድምጽ አገኙ አላገኙ የታወቀ ነገር የለም ሲሉ አስቀምጠዋል/ገጽ 3 አንቀጽ 6/ ። የኢህአዴግ ይቅር ቅንጅት አዲስ አበባ ማሸነፉን፤ ብሎም ከንቲባ ምክትል ከንቲባ ወዘተ መሰየሙን ህብረቱ አልተቀበለም? በ21 ኛው የአንተርኔት ምዕተ ዓመት ላይ ሆነው አልሰሙም አይባልም። ቢያንስ ሜሪላንድ ከሄዱት ዶ/ር በየነ ጴጥሮሰ መራራ ጉዲና ወይም አቶ ሙሉ መጃ እና ሌሎች የልዑኩ አባላት የሚያረዳ ጠፋ።

የሚያረዳ ያልኩበት ምክንያት፣ የሚያበሰር እንዳልል በዶ/ር ብርሃኑ በአለ ሲመት ላይ ህብረቶች አለመገኘታቸው የአዲስ አበባ ድድ ማስጫዎች ጉምጉም ሆኖ በመሰንበቱ ነው።

የብሄራዊ ዕርቅ ሃሳቦች ተቀባይነት ካላገኙ /ኢህአዴግ ውድቅ ማድረጉ ቅንጅትም የተደገሰለትን አላወቀ በአጋርነት መቆሙ ሳይዘነጋ /ህብረቱ በ15 ቀናት ውስጥ በጠቅላላው ተቃዋሚ ድርጅቶችን፣ አለም አቀፍ ታዛቢዎች የአገር ሽማግሌዎች ምኑቅጡ ሌሎችም የሚሳተፍበት አስቸኳይ አገር አቀፍ ጉባዔ ለመጥራት ፍላጎት እንዳለው ብሎም ዘርፈ ብዙ ሰልፍና ለህግ ያለመገዛት /Civil disobedience/ ድርጊቶችን ለመፈጸም እያሴረ ነው።

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ የጦርነት አውርድ ትርምሳችሁን አይፈልገውም። የኛ ምኞት ተቃዋሚዎች ከገቡበት እንቆቅልሽ እንድትወጡ ነው። ተቃዋሚዎች ከዕውነታ ጋር መታረቅ ይኖርባቸዋል።